# ከዋናው መስሪያ ቤት የመጡት እንግዳ

## ክፍል አራት

ከበልጅግ አሊ

ሊቁ በረንዳው ላይ ተቀምጦ ስለእሱና ስለ ጌጤ ትዳር አጀማመር ማሰላሰሉን አንዳንዴ ኮስተር አንዳንዴ ደግሞ ትክዝ እያለ ቀጠለ። የዛን ለት ለመጀመሪያ ጊዜ ከጌጤ ጋር አንሶላ ከተጋፈፈ በኃላ ከናስር ጋር ጫት እንደሚቅሙ ቤቱን እንድታዘጋጅ ነግሯት በቀጥታ ከእሁድና ከማርያም ቀን በስተቀር ሁል ግዜ ተዘግቶ ከሚከርመውና እሮብ ገበያ ውስጥ ከሚገኘው ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሄዶ ደረጃው ላይ ተቀምጦ የጌጤን ክብር መድፋሩ ትክክል ይሁን ስህተት ግራ ገብቶት ያወጣና ያወርድ ጀመር። በአንድ በኩል ጌጤን ወዲታል በሌላ በኩል ደግሞ ለስደት የዳረገው ችግር ሲቃለልለት ወደ አዲስ አበባ ሲሄድ ምን እንደሚሆኑ፣ የት እንደሚያርፉ ፣ ቤተሰቦቹ ምን እንደሚሉት አሰበ፣ ብዙም ሳይቆይ ወደ አዲስ አባባ ከተመለሰ ከጌጤ ጋር አብረው ለመሄድ የሚከለክለው ጉዳይ ስለሌለ ሰለእሱ ማሰብ ትቶ እንዴት አድርጎ ሠርጋቸውን እንደሚያዘጋጅ ማሰላሰል ቀጠለ።በዛም ብዙ አልገፋም። ናስር ይህንን ጉዳይ በጣም ስለሚደግፍ እሱ ተሯሩጦ ሠርጉን እንደሚዘጋጀው ገብቶታል። አሁን ግን ወደ እዚህ ቤተ ክርስቲያን ያመጣው ሌላ ጉዳይ እንደሆን ግን አላጣውም።ፅጌሬዳ ነች።

ፅጌሬዳን ምንም እንኳ በሕይወት ባትኖርም በየቀኑ እንደሚያስባት፣ ሲከፋው የከፋውን ፣ ሲደሰት ደስታውን እንደሚካፍላት ሁሉ ዛሬም ከጌጤ ጋር የደረሰበትን ሁኔታ ለመግለፅ ብቸኝነት ስለሚያስፈልገው ሁል ግዜ እንደሚያደርገው እቤተክርስትያኑ ደረጃ ላይ ተቀምጦአል።

ፅጌረዳ የሊቁ ጓደኛው የነበረች ስትሆን በቀይ ሽብር እንደተገደለች እዚሁ እሮብ ገበያ ከመጣ በኋላ ነው ያወቀው። ፅጌሬዳን ወደ ስደት ከመምጣቱ በፊት አብራው እንድትሰደድ ጠይቋት ነበር።ሁኔታውንም ከእሷ አልፎ እናቷን ቢነግራቸው፣ አደገኛነቱንም ቢያስረዳቸው፣ እናትየው ግን ቀበሌ የሚሰራ ሁነኛ ሰው ስላለ እሱ እንደሚያድንላቸው ስለተማመኑ ሊቀበሉትና ከእርሱ ጋር ሂጂ ብለው ሊገፋፉአት አልፈለጉም። ይህ አልሆን ሲለውና እሷም ከአለእናቷ ፍቃድ መሄድ ስላልፈለገች ጥሏት ሊሄድ ቆረጠ።

ለእናትየው ግድየሎትም እኔ አድናታለሁ ብሎ ቃል የገባላቸው አብዮት ጥበቃ ቃሉን አጥፎ እንዲያውም የበለጠ የሷ ከሳሽና መርማሪ ሆኖ ብዙ ካሰቃያት በኃላ በቀይ ሽብር እንድትመታ ወተወተ።አንድ ቀን ጠዋት እናቷ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲሄዱ ያ የሚምረው ሰውነቷ በግርፊያ ብዛት በልዞና አባብጦ፣በደም አበላ ተለውሶ፣ አንድ ነገር መናገር እንደፈለገች ከንፈሮቿ ገርበብ ብለው እቤታቸው አጠገብ በሚገኘው መንገድ ላይ ወድቆ እንዲያገኙት አደረገ።

ሊቁ ጽጌሬዳን በቀይ ሽብር መመታቷን እንደሰማ እያለቀስ ደምሽን እበቀላለሁ ብሎ ቃል የገባው አሁን ትዝ አለው።።ቤተክርስትያኑ ደረጃ ላይ ተቀምጦ አይኑ በእንባ ተሞልቶ።ጽጌረዳ በቅርብ የምትገኝ ይመስል በሃሳቡ እያነጋገራት፦

„ ሆዴ እንደምን ከርመሻል። እኔ መቼስ የምንቀሳቀስ ስለሆንኩ በየእለቱ አዲስ ነገር ይገጥመኛል። አየ የዛሬው ግን ከሁሉም በፊት አንቺ መስማት አለብሽና ላንቺ ለመናዘዝ ብዬ ነው የመጣሁት።“

„ሆዴ እንዴት ነሽ።አፈሩን ለመድሽው?ኑሮው ተስማማሽ ልበል እንጂ መቸሽ ምን ማለት እችላለሁ። እነዚያ የሚያምሩትት አይኖችሽ ፈረሱ? ያ ለስላሻ ሰውነትሽስ ተበጣጥቆ ወደቀ? እሱን እሱን ሳስብ ያንችን ገዳዮች ቀን ወጥቶልኝ ባገኛቸው ምን እንደማደርጋቸው አላውቅም። ግን ምን ይሆናል ዛሬ ተረታሁልሽ። ድሮ ገና አንድ ቀን ትረሳኛለህ ያልሽው ሊጀመር ነው መሰል ልቤን ፍራት ፍራት አለው“።

ሆዴ ፈራሁ እናቴ እንዴት ብዬ ልንገርሽ? ዛሬ የሆነውን ሁሉ እንዴት ብዬ ላስረዳሽ እንዲህ በጥቂት አመታት አንቺን ፍቅሬን ትቼ ሌላ ሰው ጋር ትሄዳለህ ብለሽ ድሮ ብትይኝ አልሰማሽም ነበር። አሁን ግን ሆነ። ሆዴ ይቅር በይኝ።ሰው ነኝ ብቸኝነቱ አጠቃኝ። ኑሮ ከበደኝ። ሰውነቴ ሰው ፈለገ። እኔም ተሸነፍኩ።

ምን ብዬ ልንገርሽ? ዛሬ ካንች እየተነጠልኩ ብቻዬን የምጓዝበትን መንገድ ጀመርኩ። ሳላስበው ከአንድ ምንም ከማታውቅ ንፅሁ ፍጡር ፍቅር ጀመረኝ። ንፅህነዋና በህይወቷ የተቀበለችው ስቃይ ልቤን በረገደው ፣ መጠለያ ስለፈለገች ላስጠልላት ቃል ገባሁላት ፣ ስቃዬን ብቸኛነቴ ስለገባትና ስላዘነችልኝ አዘንኩላት። ሌሎች እንደገና እንዳያሰቃይዋት ልከላከላት ቃል ገባሁላት።

ሆዴ ለካስ ስቃይም ሆነ መከራ ከቦታ ቦታ ይለያያል። ምን እንዳለችን ታውቂያለሽ። ለአንተ ስቃይ የመጀመሪያህ ስለሆነ ከብዶሃል ለኛ ግን በስቃይ ተወልደን ፣ በስቃይ ስለኖርን ድሎትን ስለማናውቅ ምንም አይመስለንም። ስቃይን እንደድሎት እንቀበለዋለን። ለእናንተ ለከተማ ልጆች ግን ገጠር መኖር እንኳ ስቃይ ነው። የከተማ ፍቅር አይንህን ሽብቦ በአጠገብህ ያለነውን ሊሳይህ ስላልቻለ እባክህ ልቤን የባሰ አታድማው ፣ አታቁስለው ፣ ተስፋ ያለው ሕያወት አታሳየኝ ፣ መውደድ እንደምችል አታስተምረኝ ፣ እባክህ እቃህን ጠቅልልና ከአጠገቤ ጥፋ ፣ ወደ ከተማህ ተመለስ ፣ እኔም ወደ ኖርኩበት ልመለስ ብላ ስቅስቅ ብላ ስታለቅስ አጠገቧ ሄጄ ላባብላት ብዬ ተሸነፍኩ፡፡ ለብዙ ግዜ ስታገል የነበርኩት ሁሉ እረሳሁት አንቺን እረሳሁሽ ፣ ቃል የገባሁትን እረሳሁት። ሆዴ ተሸነፍኩ፣ አፈቀርኩ ይቅር በይኝ። ብሎ ሰውነቱን ቀሎት ወደ ቤቱ ሄደ።

ያ የመጀመሪያው ቀን አሁንም ትዝ ይለዋል።ዛሬ እቤቱ በረንዳ ላይ ተቀምጦ በትዝታ ማዕበል ውስጥ ተዘፍቆ እንደገና ሲንሰቀሰቅ ዛሬ ደግሞ ምን ሆነሃል? ለምን ታለቅሳለህ? ብላ ጌጤ ከሃሳቡ ቀሰቀሰችው። ሊቁም ምንም አደል ብሎ ከሃሳቡ ወጥቶ የቀረበለትን ሻይ ጠጥቶ እንደገና ስለ ጉመሮና ስለ ሰሞኑ ሁኔታ ማሰብ ጀመረ።

ሊቁ ገረመው ሰሞኑን ከጠጅ ቤት መጥፋቱ ለምን ይሆን ብሎ አሞት ይሆን፣ ችግር ገጥሞት ይሆን ብሎ ሲጨነቅ ሲጠበብ ነበር የሰነበተው ገረመው ግን ሌላ ምክንያት ነበረው።

ገረመው እቢሮው ተቀምጦ አሳብ ውጦታል። በአንድ በኩል የሻይ ተክሉ እጣ ምን እንደሚሆን ያሰላስላል። ተመልሼ ጎሬ ፣ ድንጋይ ላይ ተቀምጬ ራፖር መፃፍ ፣ የተጣላ ሰው መፈለግ ፣ ባልና ሚስት ማፋታት ፣ ዳግም አላደርገውም እያለ ይፎክራል።ይህንን ሃሳቡን ደግሞ የማታው የሞቀ የጠጅ ቤቱ ጨዋታ ደግሞ ሌላ ሃሳብ ይሆንበታል። ዛሬ ምን ልንገራቸው ። ምንም አዲስ ነገር የለም ።ከሌለ ደግሞ እያለ የደበቅኃቸው ይመስላቸዋል። ትላንት የሚጠብቁት ሰውዬ አልመጡም ስላቸው ሽማግሌው አባ እሸቱ ምን ያህል እንደተበሳጩ አይቸዋለሁ። አቶ አስፋውማ መቱ ኦሞ ቡና ቤት ውስጥ መሽጓል አሉ። እዛ አድሮ ካልዋለ ወደ ጉመሮ አይዘልቅም።

አቶ አስፋው በድሎት የኖረ ሲሆን ምንም ጊዜም ቢሆን ከራሱ ምቾት በስተቀር ሌላ ለማንም የማያስብ ግለሰብ ነው። መንግስት በተለያየ ቦታ ሞክሮት አልችል ቢል እንደ ቅጣትም እንደ ማረፊያም የሻይ ልማትሥራ አስኪያጅ አደርጎ መድቦት ነበር። ያኔ እሱ ሻይ ልማት የተመደበ ግዜ የሻይ ልማቱ አነስተኛ በመሆኑ እስቲ ይህን እንኳ ይቻለው ተብሎ ነበር እዛ የተመደበው። አቶ አስፋው ግን ምኑም አልሆንለት ሰላለው ሥራ እንደበዛበት ሰው ለመጣ ለሄደው ሥራውን ሲማርር ሁሉም አይ አስፋው እቺም ሰራ ሆና ከበደችው እየሉ ያሙት ነበር።

በኃላም ሻይ ልማት ብድር ተሰጥቶት እንዲስፋፋ ሲደረግ በአቶ አስፋው ላይ ሌላ ሥራ በቃኝ የማይል ሥራ አስኪያጅ ተመድቦለት ሻይ ተክሉ መስፋፋ ጀመረ። አዲሱ ሰራ አስኪያጅ የመጀመሪያው ሥራው አቶ አስፋውን ጥግ ማስያዝ ነውና የክፍል አላፊ አደርጎ እድሜው ሳይደርስ የሚጦርበት ቦታ አስቀመጠው። የአቶ አስፋው ሥራ አንዳንዴ አዲስ አበባ ሲሰለቸው ወደ ከፋና ኢሊባቡር ብቅ በማለት ጉብኝት አድርጎ መመለስ ነው።ከአዲስ አባባ ሲመጣ ወደ ጉመሮ የሚደርሰው ጅማና መቱ ላይ ሆቴል ይዞ አርፎ ነው ። በፈጣን መኪና የአንድ ቀን መንገድ የሆነው ጉዞ ለአቶ አስፋው ከፈጠነ ሶስት ቀን ይወስድበታል። አቶ አስፋው ምን ግዜም ጉመሮ ሲገባ የመንገዱ መጥፎነትንና ወገቡን እንደቆረጠው ማውራት ያበዛል። ከዛም የሁለት ቀን እረፍት እንደሚስፈልገው ተናግሮ እንግዳ መቀበያ

ከተዘጋጀው ቤት ውስጥ እረፍት ያደርጋል። በዚህ ሁለት ቀን ውስጥ የሚፈልገው እየቀረበለት እራሱን እየጠገነ ያርፍና ድካሙ ሲወጣለት ሻዩን ለመመልከት ይመጣል።

አቶ አስፋው ለሥራ መዘጋጀቱን የሚያስታውቀው ነጭ ኮፍያ ካኪ ሸሚዝና ሱሪ ከለበሰ ነው። ይህንን ግዜ ከአቶ አስፋው ቁጣ የሚያልፈው ከቆመ የተቀመጠ ፣ ከተቀመጠም የተኛ ብቻ ነው። አለበለዚያ ግን ያየውን ሁሉ እየሰደበ እሱ ባይኖር ሁሉም ነገር ይበላሽ እንደነበረ እየጮኸ ፣ ያልተበላሸውን ለማስተካከል ሲሮጥ ፣ የተባላሸውንና ብዙ ሥራ የሚስፈልገውን እንዳላየ ሲልፍ ይውላል። በየቀኑ ደግሞ አቶ አስፋው የሰራውን ቀምሞ ጽፎ ማስተላለፍ የገረመው ስራ ነው። አቶ አስፋውን ክቦ አሳምሮ ገረመው ሲጽፍ አቶ አስፋው ደግሞ እንዳንተ አይነት አዋቂ ሰው እዚህ ምን ይሰራል ይለዋል። ገረመው ምንም ከማይወጣው ከአቶ አስፋው እንኳ ሳይቀር የጠጅ መጠጫውን በጥሩ ፅህፈቱ ሊያገኝ ችሏል።ቢሆንም ገረመው የአቶ አስፋው ምስጋና ባፍንጫው ይውጣ እንጂ እሱ ባይመጣ ደስ ይለዋል፡፡ እንዲውም አሁንማ ሻይ ልማቱ ሊዘጋ ነው ተብሎ በሚወራበት ግዜ አቶ አስፋው ያንን በሚመለከት ፃፍ ቢለው አሞኛል ብሎ ላለመጻፍ ወስኗል።

አቶ አስፋው ጉመሮ ካሉት ሠራተኞች ጋር የሚግባባበት ገዳይ የለም። መጥቶ እስከሚሄድ ድረስ ግቢው የሞት ጥላ እንዳንዣበበት በጣም ይከብዳል።የሻዩን ልማት በሚጎበኝበት ግዜ ደግሞ ወደ ሻዩ ውስጥ ከመግባት በመኪና እየዞረ መመልከትን ይወዳል። በመኪናም ሆኖ ጉብኝቱ ቶሎ ይሰለቸውና ወደ ቢሮ ይመለሳል። እቢሮ ገብቶ አንዱን ሲያማ አንዱን ሲክብ ይውልላ። ምሳ ሰአት ሲደርስ ጠዋት እንዲዘጋጅለት ያዘዘውን ተካ የሚባል ወጥ ቤት አንዴ እያመሰገነ ፣አንዴ ደግሞ እየወቀሰ ለመብላት ይሄዳል። ምሳውን በልቶ ቡናውን ጠትቶ ትንሽ ከተኛ በኃላ ሁል ግዜ ከእጁ የማይጠፋውንና አንብቦ የማይጨርሰውን የሃሮልድ ሮቢንሰንን መጽሐፍ ይገልጥና ይመለከታል። መጸሐፉ ድሮ ፈረንጆቹ እዛ ቤት ሲኖሩ ገዝተው ያስቀመጡት ነው። አንዳንድ ሰዎች የእንግዳ ቤቱን እቃ አንድ በአንድ አቶ አስፋው እየወሰደ እንደለወጠው ያወራሉ። ለምሳሌ ሶፋውን አዲስ አባባ እንዲታደስ ይላክ ብሎ ካዘዘ በኃላ ታድሶ ሲመለስ ሶፋው ቀይሮ ሌላ አነስተኛ ፎቴ እንደላከ ይናገራሉ። አቶ አስፋው በጠቅላላው ሰራተኛ በጣም የተጠላ ሰው ነው። አሁን ደግሞ የሻይ ልማቱን የወደፊት እድል ለመወሰን እሱ መላኩ ሁሉንም ሠራተኛ በጥብጦታል። ምክንያቱም አቶ አስፋው ሻይ ልማት በአዲሱ ስራ ሥስኪያጅ ምክንያት ከሰረ። እኔ ብሆን ኖሮ እንዲህ አይሆንም ብሎ ለማውራት እንደሚቸኩል የታወቀ ነው።

ገረመው ዛሬ ምንም የማወራው አዲስ ነገር ስለሌለ ዛሬ ጠጅ ቤት ዕሮብ ገበያ ሄጄ የሰውን ጨቅጭቅ አልሰማም እያለ ፣ በአንድ በኩል ደግሞ በአንድ አስተማሪና በሊቁ መካከል ትላንት ተነስቶ የነበረውን ጭቅጭቅ ትዝ አለው። ጨዋታው የተጀመረው እንደተለመደው ጉመሮ ይዘጋል ወይስ አይዘጋም በሚለው ነው። ሠራተኞቹ እና መምህራኖቹ በዚህ ላይ የጦፈ ክርክር ሲደርጉ ግማሹ መንግስት ለሰራተኛው የቆመ ስለሆነ አይዘጋውም ሲል ግማሹ ደግሞ መንግስት ስለ ሰራተኞቹና ስለቤተሰቦቻቸው ምንም ደንታ የለውም ይላሉ ። ሁሉም በየቦታው ተዘጉ የተባሉ የመንግስት እርሻዎችን እያነሱ መጨዋወትን ላይ በነበሩበት ግዜ አንድ ከሊቁ ጋር የሚያስተምር አስተማሪ ዋነኛ ተናጋሪ ሆኖ እየደጋገመ አሳብ ይስጥ ነበር።ሊቁ ከዚህ ከሥራ በባልደረባው ጋር ምንም መግባባት ስሌለለው ሬዲዮኑን እየጎረጎረ ፣ጠጁን እያጣጣመ ፣ አለፍ አለፍ እያለ አባ እሸቱን ይጫወቱ እንጂ እያለ ይጋብዛቸው ነበር።

አባ እሸቱ አጭር ሲሆኑ በሻይ ተክሉ ውስጥ ለረጅም ግዜ ስለሰሩ አሁን ሻዩን ለማድረቅ ለሻዩ ፋብሪካ ለሚያስፈልገው እንጨት አዲስ ሻይ ሲተከል ከሚመነጠረው ደን ውስጥ በሞተር በሚሰራ መጋዝ በመጠቀም እንጨት ለሚያቀበርቡት ክፍል ካቦ ሆነው ይሰሩ ነበር። አባ እሸቱ እረጅም ጢም ሲኖራቸው ታታሪ ከመሆናቸው የተነሳ በሻይ ተክሉ ውስጥ ከበሬታን ያገኙ ናቸው። አባ እሸቱ የከፉቸውን ጊዜ ሲናደዱ ከመናገር ጢማቸውን እየፈተሉ መተከዝን ይወዳሉ። በተለይ አንድ ሰው የማይጥም ነገር ከተናገረ እንደዚሁ ጢማቸውን በመግመድ አለመስማማታቸውን ሲገልፁ ምን አለባት መጠጡ ከበዛና አባ እሸቱ ሞቅ ካላቸው እያንዳንዱን እያስታወሱ ይሳደባሉ።

በዚህ ቀን አባ እሸቱ እንደተለመደው ጢማቸውን እየፈተሉ አስተማሪው የሚናገረውን ሲሰሙ ነበር ። ሊቁ ሁኔታውን ስለሚያውቀው አባ እሸቱን ተጫወቱ ብሎ ቢጋብዛቸውም አባ እሸቱ ግን የአስተማሪውን ችኩልነት እየተመለከቱ፣ እየተበሳጩ ጠጃቸውን መጠጣት ቀጠሉ። ጊዜው እያመሸ፣ ጨዋታው ምቅ ደመቅ እያለ አባ እሸቱም የጠጁ ሞቅታ እየተስማማቸው ሄደ።

አስተማሪው ምንም ሳያሰበው አባ እሸቱ ጮክ ብለው ቅድም ስትናገር መንግስት የነቃ ፣ የተደራጀና ፣የታጠቀ ፣ ወዝ አደር ነው የሚፈልገው ብለሃል።ከዛም ቀጥለህ እርሻ ተክሉ አብዮቱን ካልጠቀመ መንግስት ሊዘጋው ይችላል ስትል ነበር። በአንተ አስተሳሰብ እኛ እስካሁን ያልነቃን የተኛን ነን ማለት ነው? ብለው ሲጠይቁት ጠቅላላ በጠጅ ቤቱ የነበረው ሰው ሁሉ የሚቀጥለውን  የአባ እሸቱን ሁኔታ ስለሚያውቁ ዝም ብለው የአስተማሪውን መልስ ይጠብቁ ጀመር።ይህን ግዜ ሊቁ ምንም ሞቅ ቢለውም አባ እሸቱ ወዴት እንደሚሄዱ ስላወቀና አስተማሪው እሱ ያስተባበረበት እንዳይመስለው ነገሩ ሳይከር ልሂድ ብሎ ሲነሳ አባ እሸቱ ሊቁ ተቀመጥ ወዳጄ ምን አስቸኮለህ አንተ ከኛ ጋር ኖረህ አብረኸን በልተህ ጠጥተህ እኛን መስለህ ፣ እኛ ስናዝን አንተም አዝነህ ፣ ስንደሰት ስቀህ ፣ ስናለቅስ አልቅሰህ ፣ መከራችንን ፣ደስታችንን ፣ኑሯችንን ኖረሃል። አሁን ታዲያ ገና ከመድረሷ ቅጠል መበጠስዋ እንዲሉ ፣ አልነቃችሁም ፣ አልተደራጃችሁም ፣ አልታጠቃችሁም እና ለአብዮቱ አትጠቅሙም ተበተኑ ብሎ ይህ ሰው ሲናገር ጥለህ ለመሄድ መነሳትህ ለምን እንደሆን ቢገባኝም ፣እኛን የማይገባንን ጉዳይ ከዚህ አስተማሪ ቢመጣ ታስረዳናለህና ታገስ አሉና አስተማሪውን ጥያቄውን እንዲመልስላቸው ትኩር ብለው ያዩት ጀመር።

አስተማሪውም አንድ የነቃ ወዝአደር አብዮቱ ቢጎዳው እንኳ  ጉዳቱን ችሎ ወደ ፊት አብዮቱ የሚሰጠውን ተስፋ ሊጠብቅ ይገባል።ስለዚህም ጉመሮ ይዘጋል ብለን ልንፈራ አይገባም። ዋናው ጉዳይ ጉመሮ አብዮቱን እስካልጠቀመ ድረስ ቢዘጋ እንኳ መናደድ አይኖርብንም ብሎ ንግግሩን ጨረሰ። አባ እሸቱ አሁን ትዕግስታቸው አልቆ አንተ እያስተማርክ ደሞዝህን እየበላህ የኛ ሕይወት መጨለሙን እየደገፍ ስትናገር ምንም አይሰማህም? የኛ አብዮቱ መጣላችሁ የምንባለው ታዲያ ምኑ ላይ ነው? እኛ ከሞትን በኋላ ነው እንዴ የሚያልፍልን ። ይህንን ነው የተማርከው ማለት ነው ብለው ጠየቁት። አስተማሪው እንደገና ሲቀበጣጥርና ሲዘበራርቅ ብዙዎቹ ሠራተኞች በጥለቻ ይመለከቱት ጀመር። ሊቁም ምንም አሳብ ሳይሰጥ ዝም ብሎ ሲመለከት ቆይቶ ጠጁን እየደጋገመ መጨለጥ ቀጠለ። ሞቅ ሲለው እየጮኸ ጎማ ሙሉ ፈስ፣ አንተ ብሎ አብዮተኛ፣ አንተ ብሎ የነቃህ፣ ማቲማቲክ ዋን ኦ ዋንን ሳትማር ስለሎጂክ የምታወራ። አንተ ምንታውቀለህ ሰለ ላብአደሩ፣ አንተ ምን ይገባሃል ስለቤተሰብ ፣ አንተ የገደል ማሚቱ ፣ የሚነግሩህ ደግመህ የምታጎላ፣ በቀቀን የሰማኸውን የምትደግም፣ ሽል እግዴ ልጅ የማትረባ፣ እያለ እየተሳደበ ወደ ቤቱ ሄደ።

ገረመው ይህንን ሲያወጣ ሲያወርድ ከጎሬ መንገድ አንድ መኪና ሲመጣ የሚያስነሳው አቧራ ታዬ። ጠቅላላ የጉመሮ አንገት ወደ ጎሬ ዞረ። ከዋናው መስሪያ ቤት የመጡት እንግዳ አንድ የራሽያ አዲስ መኪናቸውን እያበረሩ ወደ ጉመሮ ቀረቡ ።

ይቀጥላል።